# ትምህርት 9

1. እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን የመፍጠር ሥራውን ፈጽሟል?

ሀ- አዎን።

2. እግዚአብሔር የጀመረውን ሥራ ሁል ጊዜም የሚፈጽመው እንዴት ነው?

ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር ፈጽሞ የማይለወጥ ስለሆነ ነው።

ለ- እግዚአብሔር ሥራውን እንዳይፈጽም ልከለክል የሚችል ምንም ነገር ስለሌለ ነው።

3. እግዚአብሔር የጀመረውን ሥራ ሰይጣንና አጋንንቱ ሊያስቆሙት ይችላሉ?

ሀ- አይችሉም።

4. ታዲያ እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ለምን ዐረፈ?

ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር ያቀዳቸውን ነገሮች ሁሉ ፈጥሮ ስለ ፈጸመ ነው።

5. እግዚአብሔር ሁሉንም ነገሮች በስንት ቀን ውስጥ ፈጠረ?

ሀ- በስድስት ቀን።

6. በመጀመሪያ ዝናብ ካልነበረ፣ እግዚአብሔር ምድርን በምን ያጠጣ ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር ምድርን ያጠጣ የነበረው ከመሬት በሚመነጭ ውሃ ነበር።

7. እግዚአብሔር የተከላት ገነት ምን ትባል ነበረ?

ሀ- የዔድን ገነት።

8. እግዚአብሔር የዔድን ገነትን የተከለው ለማን ነበር?

ሀ- ለአዳም።

9. እግዚአብሔር ለአዳም ገነት የተከለው ለምን ነበር?
ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር አዳምን እጅግ ስለሚወደው ነው።

10. እግዚአብሔር አዳምን «በገነት ውስጥ ላስቀምጥህ?» ብሎ ያልጠየቀው ለምንድን ነው?
ሀ- ምክንያቱም አዳምን የፈጠረው እግዚአብሔር ስለሆነ ነው አዳም የእግዚአብሔር ነው።

11. እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው ስለ ፈጠረ ሁሉም ሰው የማን ነው?
ሀ- ሁሉም ሰው የእግዚአብሔር ነው።

12. በዔድን ገነት መካከል እግዚአብሔር የተከለው የመጀመሪያው ዛፍ ምን ይባል ነበር?
ሀ- የሕይወት ዛፍ።

13. እግዚአብሔር በዔድን ገነት መካከል የሕይወትን ዛፍ የተከለው ለምን ነበር?
ሀ- እግዚአብሔር አዳም ከዛፉ በልቶ ለዘላለም እንዲኖር ፈልጎ ነበር።

14. እግዚአብሔር በዔድን ገነት መካከል የተከለው ሁለተኛው ዛፍ ምን ይባል ነበር?
ሀ- መልካምና ክፉን መለየት የሚያስችል የዕውቀት ዛፍ ነበር።

15. መልካምና ክፉን መለየት የሚያስችለውን የእውቀት ዛፍ በተመለከት እግዚአብሔር ለአዳም የሰጠው ትእዛዝ ምን ነበር?
ሀ- እግዚአብሔር አዳም የዛፉን ፍሬ እንዳይበላ አዘዘው።

16. አዳም መልካምና ክፉን መለየት የሚያስችለውን የእውቀት ዛፍ ከበላ ምን ይደርስበታል?
ሀ- አዳም ይሞታል።

17. ሞት ምንድን ነው?

ሀ- የሕይወት ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር መለየት።

ለ- የነፍስ ከሥጋ መለየት።

ሐ- ተለይቶ በዘላለሙ የእሳት ባሕር ውስጥ መጣል።

- እግዚአብሔር አዳምን ከፈጠረ በኋላ ምን እንደ ተናገረ እናንብብ

ዘፍጥረት 2፡18

18- ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ «ሰው ብቻውን መሆኑ መልካም አይደለምና የሚስማማውን ረዳት አበጅለታለሁ» አለ።

- እግዚአብሔር አዳም ብቻውን መኖር እንደሌለበት ወሰነ።
- እግዚአብሔር ለአዳም ሚስት ሊፈጥርለት ወሰነ።

- እግዚአብሔር አዳምን ምን እንደሚፈልግ አልጠየቀውም።

- እግዚአብሔር ራሱ ለአዳም ሚስት ሊፈጥርለት ወሰነ።
- እግዚአብሔር ለአዳም ሚስትን ሊፈጥርለት የወሰነው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር አዳምን እጅግ ስለሚወደው ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር አዳም ብቻውን እንዳይሆን ስለፈለገ ነው።

ዘፍጥረት 2፡19-20ሀ

19- እግዚአብሔር አምላክ የዱር አራዊትንና የሰማይ ወፎችን ከምድር ሠርቶ ነበር፤ ለእያንዳንዳቸውም ምን ስም እንደሚያወጣላቸው ለማየት ወደ አዳም አመጣቸው። አዳም ሕይወት ላላቸው ፍጡራን ሁሉ ያወጣላቸው ስም መጠሪያቸው ሆነ።

20- ስለዚህ አዳም ለከብቶች፣ ለሰማይ ወፎች፣ ለዱር አራዊት ሁሉ ስም አወጣላቸው።

- በመጀመሪያ እግዚአብሔር አዳምን የዓለም ሁሉ አለቃ አድርጎ ሾመው።

- በመጀመሪያ እግዚአብሔር ለእንስሳት ሁሉ አለቃ አድርጎ ሾመው።

- እግዚአብሔር አዳም ለእንስሳት ሁሉ ስም እንዲያወጣላቸው ጠየቀው።

- አዳም ለሁሉም እንስሳት ስም አወጣላቸው።

- ነገር ግን አዳም በምድር ላይ ብቸኛ ሰው ነበረ።

ዘፍጥረት 2፡20ለ

20- ይሁን እንጂ ለአዳም ተስማሚ ረዳት አልተገኘለትም ነበር።

- እግዚአብሔር ሰዎችንና እንስሳትን የፈጠራቸው አንድ ዓይነት አድርጎ ነው?

- አይደለም።

- እግዚአብሔር እንዴት ነው ሰውንና እንስሳትን የተለያዩ አድርጎ የፈጠራቸው?

- እግዚአብሔር እንስሳትን በራሱ አምሳል አልፈጠረም።
- እግዚአብሔር በራሱ አምሳል የፈጠረው ሰውን ብቻ ነው።

- ሰዎች እግዚአብሔርን ማወቅ ይችላሉ እንስሳት ግን እግዚአብሔርን ማወቅ አይችሉም።

- ሰዎች እግዚአብሔርን መውደድ ይችላሉ እንስሳት ግን እግዚአብሔርን መውደድ አይችሉም።

- ሰዎች እግዚአብሔርን መምረጥ ይችላሉ እንስሳት ግን እግዚአብሔርን መምረጥ አይችሉም።

- አዳም ስለ አንድ ነገር ሲያስብ እንስሳት ከእርሱ ጋር እንዲያስቡ ሊጠይቃቸው ይችላል?

- አይችልም።
- አዳም ሲደሰትም ሆነ ሲያዝን እንስሳት የደስታውም ሆነ የኀዘኑ ተካፋይ እንዲሆኑ መጠየቅ ይችላል?

- አይችልም።
- አዳም አንድን ነገር ማድረግ ቢፈልግ፥ እንስሳት ከእርሱ ጋር ያንን እንዲያደርጉ መጠይቅ ይችላል?

- አይችልም።

- እንስሳት ለአዳም የሚመቹ ረዳት ነበሩ?
- አልነበሩም።

- ለአዳም ከእርሱ ጋር የሚነጋገር ምቹ ረዳት ያስፈልገዋል።
- እግዚአብሔር አዳምን ስለ ወደደ ለአዳም ሚስትን ሊፈጥርለት ወሰነ።

- አዳም ለራሱ ሚስትን መፍጠር ይችል ነበር?
- አይችልም።

- ሰይጣንና አጋንንቱ ለአዳም ሚስት መፍጠር ይችሉ ነበር?
- አይችሉም።

- ለአዳም ሚስትን መፍጠር የቻለው ማን ብቻ ነበር?
- እግዚአብሔር ብቻ ነበር።

- አንድ ቀን እግዚአብሔር ለአዳም ሚስት ፈጠረለት።

ዘፍጥረት 2፡21-22

21- እግዚአብሔር አምላክም በአዳም ላይ ከባድ እንቅልፍ ጣለበት፤ አንቀላፍቶም ሳለ ከጐኑ አንዲት ዐጥንት ወስዶ፣ ስፍራውን በሥጋ ሞላው።

22- እግዚአብሔር አምላክ ከአዳም የወሰዳትን ዐጥንት ሴት አድርጎ ሠራት፤ ወደ አዳምም አመጣት።

- ለአዳም ሚስትን መፍጠር የቻለው እግዚአብሔር ብቻ ነበር።

- የእግዚአብሔር ኃይል ፈጽሞ አያልቅም።
- እግዚአብሔር መሥራት የማይችለው ምንም ነገር የለም።

- እግዚአብሔር የመጀመሪያዋን ሴት ፈጥሮ፥ ለአዳም ስጦታ አድርጎ ሰጠው።

- አንድ ሰው ታላቅ ስጦታ ቢሰጣችሁ ያንን ስጦታ በጥሩ ሁኔታ ትጠብቃላችሁ?

- አዎን።
- አንድ ሰው ላም ቢሰጣችሁ ያችን ላም በጥሩ ሁኔታ ትጠብቁአታላችሁ?

- አዎን።
- አንድ ሰው መኪና ቢሰጣችሁ መኪናዋን በጥሩ ሁኔታ ትይዛላችሁ?
- አዎን።

- እግዚአብሔር የመጀመሪያዋን ሴት ፈጠሮ፥ ለአዳም ትልቅ ስጦታ አድርጎ

ሰጠው።

- እግዚአብሔር አዳም ሚስቱን በጥሩ ሁኔታ እንድንከባከባት ይፈልጋል።

- እግዚአብሔር አዳም ሚስቱን እጅግ በጣም እንዲወዳት ይፈልጋል።

- እግዚአብሔር ሚስት በሰጠው ጊዜ አዳም የተናገረውን እናንብብ፡-

ዘፍጥረት 2፡23-24

23- አዳም እንዲህ አለ፤ «እነሆ፤ ይህች ዐጥንት ከዐጥንቴ፣ ሥጋም ከሥጋዬ ናት። ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል።»

24- ስለዚህ ሰው ከአባቱና ከእናቱ ተለይቶ ከሚስቱ ጋር ይጣመራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።

- እግዚአብሔር ሴትን ለወንድ የፈጠረለት እንዲጋቡ ነው።
- እግዚአብሔር ሴትን ለወንድ የፈጠረለት አብረው እንዲኖሩ ነው።
- እግዚአብሔር ሴትን ለወንድ የፈጠረለት ልጆችን እንዲወልዱ ነው።

- እግዚአብሔር የሚሠራው መልካም ነው።

- እግዚአብሔር የሚሠራው ሁሉ ፍጹም ነው።

- ምክንያቱም መልካምና ፍጹም እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔር ክፉ የሆነ ምንም ነገር አያስብም።

- እግዚአብሔር ምንም ዓይነት ክፉ ነገር አይናገርም።
- እግዚአብሔር ምንም ዓይነት ክፉ ነገር አያደርግም።

- አዳም ትልቅ ስጦታ፥ ሚስትን በመቀበሉ የተደሰተ ይመስላችኋል?

- አዎን።
- አዳም በጣም ደስተኛ ነበር።

- የአዳም ሚስት ስም ማን ነበር?

- የአዳም ሚስት ስም ሔዋን ነበር።

ዘፍጥረት 2፥25

25- አዳምና ሚስቱ፣ ሁለቱም ዕራቁታቸውን ነበሩ፤ ይሁን እንጂ አይተፋፈሩም ነበር።

- በመጀመሪያ አዳም ሐፍረት አልነበረውም።

- በመጀመሪያ ሔዋንም ሐፍረት አልነበራትም።

- በመጀመሪያ እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ፍጹም አድርጎ ፈጠራቸው።

- በመጀመሪያ አዳምና ሔዋን ምንም ዓይነት ክፉ ነገር አያውቁም ነበር።

- በመጀመሪያ አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር በሕብረት ኖሩ በጣምም ደስተኞችም ነበሩ።